Kolleejjii Giloobaal, Kaampaasii Amboo
ግሎባል ኮሌጅ አምቦ ካምፓስ
Global College, Ambo Campus
Location: Region_ Oromia,Zone_ West Shoa, Town_ Ambo
Address: +251-920-65-28-50/ 0112609437/0112609327 Fax: 0112609437
Web site: www.globalcollege.edu.et E-mail: globe@globalcollege.edu.et P.O.Box ✉480

Lakk/ቁጥር/ Ref. No/: GC/1702//2017
Guyyaa/ቀን /Date/:23/07/2017 E.C April 01, 2025 G.C

ለረጅስትራር ክፍላችን

<u>አምቦ</u>

Received: ቀን Hunde G. 26/07/17

ጉዳዩ፡ <u>የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመግቢያ መቁረጫ ነጥብን ይመለከታል።</u>

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ በቀን መጋብት 17 2017 ዓ.ም ቁጥር 9/256/640/11 ከትምህርት ሚኒስቴር በተጻፈዉ ደብዳቤ መሰረት የየዓመቱ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ ተሰንዶ ተዘጋጀቷል።

ስለሆነም የረጅስትራር ክፍላችን ተማሪዎችን በምቀበልበት ወቅት በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጅዉን የየዓመቱ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ መሰረት በማደረግ እንዲሆን እያሳሰብኩ በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጅዉን የየዓመቱ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ ከዚህ ደብዳቤ ጋር በ 23 ገፅ አባሪ ተያይዟል።

ከሠላምታ ጋር።

Global College Ambo Campus
ግሎባል ኮሌጅ አምቦ ካምፓስ

Darajjee Baqqalaa Gulummaa
ደረጀ በቀለ ጉሉማ
Dereje Bekele Gulima
President
ፕሬዝዳንት



Telegram: https://t.me/Globalcollegeofficial/
Facebook: https://www.facebook.com/Global-College-Official
Website: www.globalcollege.edu.et

Global College
*We are Dedicated to Serve our Community!*

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፖ. ሳ.ቁ 1367፥ አራዳ ክፍለ-ከተማ
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

መጋቢት 1 7 2017

ቀን/DATE:

ቁጥር/REF NO: 9/256/641/11

ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመግቢያ መቁረጫ ነጥብን ይመለከታል

ቀድሞ በነበረው የትምህርት ፖሊሲ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ተማሪዎች የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከወሰዱ በኋላ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመግባት በየዓመቱ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ ይቀመጥ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ መረጃ አያያዝ ለአሰራር በሚያመች እና ለተገልጋዮች ጥያቄ መልስ በሚሆን መልኩ ተሰንዶ ባለመቀመጡ የቅሬታ ምንጭ ሆኖ ቆይቷል፡፡


ስለሆነም የየዓመቱን የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች (ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ በወቅቱ ከተፃፉ ደብዳቤዎችና ሰርኩላሮች) በማሰባሰብና በማደራጀት ለደንበኞች አገልግሎት ለመስጠት በሚያመች መልኩ ተሰንዶ በዚህ ደብዳቤ አባሪ የተደረገ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ኮራ ጡሹኔ ጉዳና
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ
- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ
- ለግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አገልግሎት ዴስክ

ትምህርት ሚኒስቴር



# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ

## (ከ1993 ዓ.ም - 2016 ዓ.ም)


**<u>የሰነዱ አዘጋጆች</u>**

1ኛ. እዮብ አየነው (ዶ/ር) (ከትምህርት ሚኒስቴር) --------------------- አስተባባሪ

2ኛ. አቶ ደረጀ ተስፋዬ (ከትምህርት ሚኒስቴር) ------------------------ ሰብሳቢ

3ኛ. አቶ አዲስ ዓለማየሁ (ከትምህርት ሚኒስቴር) ------------------------ ፀሃፊ

4ኛ. አቶ ፍቅረማርያም ብሩ (ከኢፌዴሪ ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን) ---- አባል

5ኛ. አቶ ጋሻው ልኬ (ከትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት) -----------አባል


የካቲት2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## 1. መግቢያ

ትምህርት ሚኒስቴር በመደበኛነት ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል አንዱ ባለጉዳዮችን በተገቢው መንገድና ስነ ምግባር በተላበሰ መልኩ ማስተናገድ ነው። በዚህ መስሪያ ቤት አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ የማህበረሰብ ክፍሎች በጣም ብዙና የተለያዩ ቢሆኑም በስፋት አገልግሎት ፈልገው የሚመጡት ተገልጋዮች ጉዳያቸው ከትምህርት ጋር የተያያዘ ነው። ከቅርብ አመታት ወዲህ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ መስሪያ ቤቶች የሰራተኞቻቸውን የትምህርት መረጃ ለማጣራት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱንና ተጠሪ ተቋማትን በተደጋጋሚ በአካልም በደብዳቤም ሲጠይቁ መቆየታቸው የሚታወስ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ግለሰቦችም የትምህርት ማስረጃቸው እንዲረጋገጥላቸውን የይረጋገጥልን ጥያቄ ሲያቀርቡ ቆይተዋል።

ከተገልጋዮች የሚቀርቡ የትምህርት ማስረጃ ይረጋገጥልኝን ጥያቄዎችን ለመመለስ ወሳኙ እና አስፈላጊው መረጃ ደግሞ በየዓመቱ የሚቀመጠው/የሚወሰነው የ12ኛ ክፍል የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ አንዱ ነው። ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት የሚያስችላቸው ውጤት ተቋማት ያላቸውን ተማሪ የመቀበል አቅምን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የመቁረጫ ነጥብ በየዓመቱ በማዕከል ይወሰን ነበር። ይህ አካሄድ በስራ ላይ ያለው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በስራ ላይ እስኪውል ድረስ ሲሰራበት ቆይቷል። በስራ ላይ ያለው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እንደሚለው አንድ ተማሪ ከአንድ የትምህርት ደረጃ ወደ ሌላ የትምህርት ደረጃ ለመሸጋገር 50% እና ከዚያ በላይ ውጤት ማስመዝገብ እንዳለበት ይገልጻል።

ይሁናን ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ ያለው የ12ኛ ክፍል የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ መረጃ ለአሰራር በሚመች እና ለተገልጋዮች ጥያቄ መልስ በሚሆን መልኩ ተሰንዶ ባለመቀመጡ ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ለመስጠት አልተቻለም። በተለይም ደግሞ 193-2001 ዓ.ም ድረስ የነበረው የየዓመቱ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ መቁረጫ ነጥብ በአግባቡ ያልተሰነደና ለመረጃነትም ሆነ ለውሳኔ የሚያገለግል ሰነድ ባለመኖሩ በተገልጋዮች ዘንድ ቅሬታን ሲፈጥር ቆይቷል። በመሆኑም ከተገልጋዮች የሚቀርቡ/የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲቻል መረጃዎችን ከተለያየ ቦታ በማፈላለግና በማሰባሰብ በዚህ ሰነድ ውስጥ በየዓመቱ የነበሩ መቁረጫ ነጥቦች ከ1993-2016 ዓ.ም ድረስ ሰነድ ተዘጋጅቷል።



Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## 2. ዓላማ

ይህንን ሰነድ ማዘጋጀት ያስፈለገው አንድም የትምህርት ስርዓት ሲቀየር በሽግግር ወቅት (ከ1993-1995) የነበረውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ነጥብ እንዲሁም ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የነበረውን የ12ኛ ክፍል የከፍተኛ ትምህርት የያመቱን መግቢያ መቁረጫ ነጥብ መረጃ በማደራጀት ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ/ለሚነሱ ጥያቄዎች በመረጃ ላይ የተመሰረተ ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ነው።

## 3. የሰነዱ አስፈላጊነት

ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ የትምህርት መረጃችን ይጣራልን ጥያቄን በመረጃ በተደገፈ መልኩ መመለስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ተጠሪ ተቋማት አስፈላጊ መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶና ሰንዶ ማስቀመጥ ስለሚጠበቅባቸው ነው። ከዚህም በላይ በዚህ በቴክኖሎጂ ዘመን ተገልጋዮች በአካል ወደ መስሪያ ቤቱ መምጣት ሳያስፈልጋቸው ባሉበት ቦታ ሆነው መረጃዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ በማስፈለጉ ነው።

## 4. የሰነዱ ወሰን

ይህን ሰነድ ከ1993 ዓ.ም እስከ 2016 ዓ.ም ድረስ በነበረው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን መቁረጫ ነጥቡ የሚመለከተው የመጀመሪያ ዲግሪ ስልጠና ለሚወስዱ ተማሪዎች ብቻ ነው።

## 5. የመረጃ ምንጭ

ይህን ስራ ለመስራት መረጃ የማሰባሰቡ ስራ መረጃው ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ የታሰቡ ተቋማት በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል። በዚህም መሰረት

- የትምህርት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት መዝገብ ቤቶች
- የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
- ብሄራዊ ቤተመዛግብት እና ቤተመጻህፍት
- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሲሆኑ በተለያዩ ጊዜያት የታተሙ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ እና በትምህርት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት የተጻፉ ደብዳቤዎች ለዚህ ስራ ዋነኛ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል።

ከመረጃ ምንጮች የተገኘውን እንደሚከተለው በሚከተለው መልኩ ተሰንዷል።



Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር

### 5.1 የመሸጋገሪያ ጊዜ (1993-1995 ዓ.ም)

በ1994 ዓ. ም ነባሩ የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ በአዲስ የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ ሲቀየር ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመግባት የሚያስፈልገው መቁረጫ ነጥብ ላይ ክፍተት እንዳይኖር በማሰብ በመስከረም 12 ቀን 1999 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ከ1993-1995 ዓ.ም ድረስ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎችን በተመለከተ በሁለቱም የትምህርት ዘርፎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወንድ 3.2 እና በላይ እንዲሁም ሴት 3.0 እና በላይ ውጤት ሊኖራቸው እንደሚገባ በግልፅ አስቀምጧል። ከዚህ በታች ውጤት ያላቸው ተማሪዎች የዲግሪ ትምህርት መማር እንደማይችሉም ያብራራል። ይህ መቁረጫ ነጥብ ለመንግስትና ለግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያገለግላል።

### 5.2 የ1996 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ

በ1995 ዓ.ም የመሰናዶ ትምህርታቸውን አጠናቀው እና ማጠቃለያ ፈተና ወስደው በ1996 ዓ.ም ከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ በነሐሴ 28 ቀን 1995 ዓ.ም በወጣውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ መሰረት 28,419 ተፈታኞች ለፈተና የተቀመጡ ሲሆን 28,206 ተፈታኞች 101 እና ከዚያ በላይ ውጤት አስመዝግበዋል። የተቀሩት 213 ተፈታኞች ከ101 በታች ውጤት ያስመዘገቡ ናቸው። ፈተናው የተያዘው ከ400 ሲሆን ከ101 በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተፈታኞች በሙሉ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዲግሪ ትምህርታቸውን መከታተል እንደሚችሉ ጋዜጣው ያብራራል። ስለሆነም በመንግስትም ሆነ በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዲግሪ ትምህርት ለመቀጠል ዝቅተኛው ውጤት 101 መሆኑን በግልፅ አስቀምጧል።

### 5.3 የ1997 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ

በ1996 ዓ.ም የመሰናዶ ትምህርታቸውን አጠናቀው በ1997 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ በሐምሌ 28 ቀን 1996 ዓ.ም በወጣውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ መሰረት በሁለቱም የትምህርት መስኮች መደበኛ ተማሪዎች ወንድ 201 እና በላይ ውጤት ያገኙ ፣ ሴት ተማሪዎች ከ176 እስከ 200 ውጤት ያገኙ፣ የታዳጊ ክልልና በማደግ ላይ የሚገኙ ዞኖች ብሔረሰብ ተወላጆች ወንድ ከ176 እስከ 200 ድረስ ውጤት ያገኙ፣ ሴት ተማሪዎች ደግሞ ከ151 እስከ 175 ድረስ ውጤት ያገኙ፣ ዓይነስውራን

ተማሪዎችም ወንድ ከ176 እስከ 200 ድረስ ውጤት ያገኙ፣ ሴት ተማሪዎች ደግሞ ከ151 እስከ 175 ድረስ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ማመልከት እንደሚችሉ ተቀምጧል። በ1997 ዓ.ም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም በተመለከተ የተቀመጠ የተለየ መቁረጫ ነጥብ ስለሌለ ለመንግስት በተቀመጠው መቁረጫ ነጥብ መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል።

## 5.4 የ1998 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ

በ1997 ዓ.ም የመሰናዶ ፕሮግራማቸውን አጠናቀው የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ አዲስ ዘመን ሐምሌ 29/1997 ዓ.ም በወጣውን ጋዜጣ መሰረት መመዘኛ ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል ውጤታቸው ለወንዶች 201 እና ከዚያ በላይ፣ ለሴቶች ደግሞ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለመግባት የሚያስችለውን መመዘኛ የወሰዱ በሙሉ፣ ለታዳጊ ክልል ብሄረሰብ ተወላጅ ተማሪዎች ለወንዶች 126 እና በላይ፣ ዓይነ ስውራን ተማሪዎች ደግሞ ከ 100 በላይ ያገኙ ተማሪዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዲግሪ ትምህርታቸውን መከታተል እንደሚችሉ ያብራራል።

ስለሆነም እዚህ ላይ የተቀመጠው መስፈርት በ1998 ዓ.ም ለከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መስፈርት ስለሆነ የመንግስትም ሆነ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን ያጠቃልላል።

## 5.5 የ1999 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ

በ1998 ዓ.ም የመሰናዶ ትምህርታቸውን አጠናቀው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ መስከረም 12 ቀን 1999 ዓ.ም በወጣውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ መሰረት ለፈተና ከተቀመጡት 42,275 ተፈታኞች መካከል 41,300ዎቹ በነባርና አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች እንደሚመደቡ ይገልጻል። በዚህም መሰረት ለሁለቱም የትምህርት መስኮች መደበኛ ተማሪዎች ወንድ 175 እና በላይ ሴት 150 እና በላይ፣ የታዳጊ ክልልና ብሄረሰብ ተወላጅ ተማሪዎች 150 እና በላይ ውጤት ያላቸው ለሁለቱም ጾታ፣ ዓይነስውራን 120 እና በላይ እንዲሁም አካል ጉዳተኞች 150 እና በላይ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመደቡ ይሆናል። ነገር ግን የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በተመለከተ የተቀመጠ የተለየ መቁረጫ ነጥብ ስለሌለ ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተቀመጠው መቁረጫ ነጥብ መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል።



Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

### 5.6 የ2000 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ

በ1999 ዓ.ም የመሰናዶ ትምህርታቸውን አጠናቀው የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ በቀን **28/01/2000 በቁጥር ት/ጠ-99/437/2000** በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት የተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኞች ወንድ 226 እና በላይ ሴት 176 እና በላይ፣ የአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር ክልልና አካባቢዎች ወንድ 201 እና በላይ፤ ማየት የተሳናቸው 176 እና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዲግሪ ትምህርታቸውን መከታተል እንደሚችሉ ይገልጻል። በሌላ በኩል ደግሞ የማህበራዊ ሳይንስ ተፈታኞች ወንድ 239 እና በላይ ሴት 176 እና በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዲግሪ ትምህርታቸውን መከታተል እንደሚችሉ ይገልጻል። ከዚህም በተጨማሪም በ1999 ዓ.ም የመሰናዶ ትመህርታቸውን አጠናቀው የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ የወሰዱና በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ያልተመደቡ ተማሪዎች በመንግስት ተቋማት በማታና በርቀት እንዲሁም በግልና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት በቀን፣ በማታና በርቀት የትምህርት ፕሮግራም መከታተል እንደሚችሉ ያብራራል።

### 5.7 የ2001 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ

በ2000 ዓ.ም በመሰናዶ ትምህርት ተከታትለው የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ ማጠቃለያ ፈተና ወስደው በ2001 ዓ.ም ከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ.ም በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ መሰረት የተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኞች መደበኛ ወንድ 128 እና በላይ ሴት 126 እና በላይ፣ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ለሁለቱም ጾታ 126 እና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተፈታኞች በዲግሪ መርሀ ግብር ትምህርታቸውን መከታተል እንደሚችሉ ይገልጻል። በሌላ በኩል ደግሞ የማህበራዊ ሳይንስ ተፈታኞች መደበኛ ወንድ 206 እና በላይ፣ ሴት 151 እና በላይ፤ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወንድ 160 እና በላይ፣ ሴት 126 እና በላይ፤ ማየት የተሳናቸው 120 እና በላይ ለሁለቱም ጾታ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርታቸውን መከታተል እንደሚችሉና በመንግስት ተቋማት በመደበኛው መርሀ ግብር ያልተመደቡ ተማሪዎች በመንግስት ተቋማት በማታና በርቀት እንዲሁም በግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቀን፣ በማታና በርቀት የትምህርት ፕሮግራም ትምህርታቸውን መከታተል እንደሚችሉ ያብራራል።

## 5.8 ከ2002 ዓ.ም -2016 ዓ.ም

በ2001 ዓ.ም የመሰናዶ ትምህርታቸውን አጠናቀው የማጠቃለያ ፈተና ከወሰዱት ጀምሮ እስከ 2013 ዓ.ም የመሰናዶ ትምህርታቸውን አጠናቀው በ2014 ዓ.ም ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመግባት የሚያስፈልገውን የመቁረጫ ነጥብ በተመለከተ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ያዘጋጀውን ሰነድ በመመልከትና ጥቃቅን ስህተቶችን በማረም የዚህ ሰነድ አካል እንዲሆን ተደርጓል። ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ማነኛውም ወደ ከፍተኛ ትምህርት ገብቶ የመጀመሪያ ዲግሪ የሚማር ተማሪ 50% እና ከዚያ በላይ ውጤት ማስመዝገብ የሚጠበቅ መሆኑ ስለተገለፀ በዚህ መንገድ የሚስተናገድ ይሆናል።

## 5.9 የአቻ ግመታን በተመለከተ

በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ አጠቃላይ ትምህርት ሀገር ውስጥ ተምረው እና የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስደው ወደ ውጭ ሀገር ሄደው ትምህርታቸውን ተከታትለው የሚመለሱ ተማሪዎች እንዳሉ ይታወቃል። የእነዚህ ተማሪዎች የመረጃ ማረጋገጥ ሂደት በተመለከተ የወቅቱን የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ የሚያሟሉ ከሆነ በውጭ ሀገር በማንኛውም የትምህርት መስክ ትምህርታቸውን ተከታትለው እና ጨርሰው ሲመለሱ በትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫና አቻ ግመታ መመሪያ ቁጥር 990/2024 ክፍል ሶስት መሰረት ያለምንም ሌላ ተጨማሪ መስፈርት እንዲስተናገዱ ይደረጋል።

# 6. በመረጃ መሰብሰብ ሥራ ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

ይህንን ሥራ እንዲሰራ የተቋቋመው ቡድን መረጃ ከየተቋማቱ ለመሰብሰብ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ወቅት ብዙ ተግዳሮቶች ያጋጠሙት ሲሆን ለመጥቀስ ያህልም፡-

1ኛ. ደራሽ ስራዎች በመብዛታቸው የተነሳ የኮሚቴው አባላት ተገናኝተው መረጃ ወደሚገኝበት ቦታ ለመሄድ የጊዜ እጥረት በማጋጠሙ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለመሰነድ ከታሰበው ጊዜ በላይ መውሰዱ፣

2ኛ. መረጃ ይገኝባቸዋል ተብሎ የታሰቡ መስሪያ ቤቶች ውስጥ መረጃዎች በተደራጀ መልኩ አለመገኘታቸው ትልቁ ተግዳሮት ነበር። ለምሳሌ የትምህርት ሚኒስትር መዝገብ ቤት ውስጥ አብዛኛዎቹ መረጃዎች ይገኛሉ ተብሎ ታስቦ የነበረ ቢሆንም በተቃራኒው በመዝገብ ቤቱ ውስጥ ከ2014 ዓ.ም በፊት የነበሩ መረጃዎችን ማግኘት አለመቻሉ፣

3ኛ. በሌላ በኩል ደግሞ መረጃ የተገኘባቸው መሥሪያ ቤቶች መረጃውን ለመስጠት ቢሮክራሲ ማብዛት፣ በተደጋጋሚ ቀጠሮ በመስጠት ማመላለስ፣ ለሚሰጡት ሰነድ ክፍያ መጠየቅ፣ የመረጃውን ኮፒ አለመስጠት እና የመሳሰሉት ተግዳሮቶች የነበሩ ቢሆንም እነዚህን ሁሉ ተግዳሮቶች በማለፍ ኮሚቴው ይህንን መረጃ ለማጠናቀር ችሏል።

ስለሆነም የ12ኛ ክፍል የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ መረጃ ያልነበራቸውን ዘመናት እና የተገኙ መረጃዎችን በተመለከተ የተቋቋመው ኮሚቴ ባደረገው ጥረት ከ1993 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ ያለውን የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ በሚከተለው መልኩ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

## ማጠቃለያ፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ የመቁረጫ ነጥብ

## (ከ193-2016 ዓ.ም)

| | የምደባ ዓመት | የተማሪ/ተፈታኝ አይነት | መቁረጫ ነጥብ በፆታ | | ውጤት የሚሰላው |
|---|---|---|---|---|---|
| 1993-1995 ዓ.ም | ምደባን አይመለከትም። ጊዜው ካለፈ በኋላ ተማሪዎች በራሳቸው እንዲደግሙ የተቀመጠ ነው። | **ተፈጥሮ ሳይንስ** | ወንድ | ሴት | |
| | | በመንግስት ተቋማት በመደበኛ | 3.4 | 3.2 | |
| | | በመንግስት ተቋማት በማታ እና በርቀት | 3.2 | 3.0 | |
| | | በግል ተቋማት በመደበኛ፣ በማታ እና በርቀት | 3.2 | 3.0 | |
| | | **ማህበራዊ ሳይንስ** | | | |
| | | በመንግስት ተቋማት በመደበኛ | 3.4 | 3.2 | |
| | | በመንግስት ተቋማት በማታ እና በርቀት | 3.2 | 3.0 | |
| | | በግል ተቋማት በመደበኛ፣ በማታ እና በርቀት | 3.2 | 3.0 | |
| 1995 ዓ.ም | 1996 ዓ.ም | ተፈጥሮ ሳይንስ | | | |
| | | በመንግስት ተቋማት በመደበኛ መርሃ ግብር | 101 | 101 | |
| | | በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | 101 | 101 | |
| | | **የማህበራዊ ሳይንስ** | | | |
| | | በመንግስት ተቋማት በመደበኛ መርሃ ግብር | 101 | 101 | |
| | | በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | 101 | 101 | |
| | | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የተፈጥሮ ሳይንስ እና ማህበራዊ ሳይንስ | | | |
| | | መደበኛ | 201 | 176 | |
| | | የታዳጊ ክልልና ከአርብቶ አደር አካባቢ ለሚመጡ | 176 | 151 | |
| | | **ዓይነስውራን** | **176** | **151** | |
| 1997 ዓ.ም | 1998 ዓ.ም | የተፈጥሮ ሳይንስ እና የማህበራዊ ሳይንስ | | | |
| | | መደበኛ | 201 | ለፈተና የተቀመጠ ሁሉም | |
| | | የታዳጊ ክልል ብሔረሰብ ተወላጅ ተማሪዎች | 126 | | |
| | | ዓይነስውራን | ከ100 በላይ | | |
| | | በግል ተቋማት በመደበኛ፣ በማታ ወይም በርቀት ትምህርትና በመንግስት ተቋማት የማታ መርሃ ግብር ትምህርታቸውን የሚከታተሉ | 12ኛ ክፍል ጨርሰው ወደ መንግስት ተቋማት ያልተመደቡ ተማሪዎች | | |
| 1998 ዓ.ም | 1999 ዓ.ም | የተፈጥሮ ሳይንስ እና ማህበራዊ ሳይንስ | | | |
| | | መደበኛ | 175 | 150 | |
| | | የታዳጊ ክልልና ብሔረሰብ ተወላጆች | 150 | 150 | |
| | | አካል ጉዳተኞች | 150 | 150 | |
| | | ዓይነ ስውራን | 120 | 120 | |
| | | አካል ጉዳተኞች | 150 | 150 | |
| 1999 ዓ.ም | 2000 ዓ.ም | የተፈጥሮ ሳይንስ | | | |
| | | መደበኛ | 226 | 176 | |
| | | የአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር ክልልና አካባቢዎች | 201 | 201 | |
| | | የማህበራዊ ሳይንስ | | | |
| | | መደበኛ | 239 | 176 | |
| | | የአርብቶ አደርና ከፊል አርሶ አደር ክልልና አካባቢዎች | 201 | 201 | |
| | | አይነ ስውራን | 176 | 176 | |
| | | በመንግስት ተቋማት መደበኛ ባልሆነ መርሃ ግብርና በግል ተቋማት ደግሞ በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ መርሃ ግብር | የመሰናዶ ትምህርት ጨርሰው ወደ መንግስት ተቋማት ያልተመደቡ | | |
| 2000 ዓ.ም | 2001ዓ.ም | የተፈጥሮ ሳይንስ | | | |
| | | መደበኛ | 128 | 126 | |
| | | ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የታዳጊ ክልል ተማሪዎች | 126 | 126 | |
| | | የማህበራዊ ሳይንስ | | | |
| | | መደበኛ | 206 | 151 | |
| | | ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የታዳጊ ክልል ተማሪዎች | 160 | 126 | |
| | | አይነስውራን | 120 | 120 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በመንግስት ተቋማት መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራምና በግል ተቋማት በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ መርሃ ግብር | ማንኛውም የማለፊያ ነጥብ አግኝቶ ወደ መንግስት ተቋም ያልተመደበ | | |
| 2001 ዓ.ም | 2002 ዓ.ም | **ተፈጥሮ ሳይንስ** | | | |
| | | መደበኛ እና የማታ | 180 | 150 | ከ500 |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና ታዳጊ ክልል ተወላጅ ተማሪዎች | 175 | 145 | |
| | | ዓይነ ሥውራን | የሉም | የሉም | |
| | | በመንግስት መደበኛ ባለሆነ ፕሮግራምና በግል ከ/ት ተቋማት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም | የመሰናዶ ትምህርት ጭርሰው በመንግስት ተቋም በመደበኛው መርሀ ግብር ያልተመደቡ | | |
| | | **ማህበራዊ ሳይንስ** | | | |
| | | መደበኛ እና የማታ | 205 | 180 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና ታዳጊ ክልል ተወላጅ ተማሪዎች | | | |
| | | ዓይነ ሥውራን | 104 | 104 | |
| | | በመንግስት መደበኛ ባለሆነ ፕሮግራምና በግል ከ/ት ተቋማት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም | የመሰናዶ ትምህርት ጭርሰው በመንግስት ተቋም በመደበኛው መርሀ ግብር ያልተመደቡ | | |
| 2002 ዓ.ም | 2003 ዓ.ም | **ተፈጥሮ ሳይንስ** | | | ከ700 |
| | | መደበኛ እና የማታ | 298 | 280 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና ታዳጊ ክልል ተወላጅ ተማሪዎች | 280 | 280 | |
| | | ዓይነ ሥውራን | የሉም | የሉም | |
| | | በመንግስት መደበኛ ባለሆነ ፕሮግራምና በግል ከ/ት ተቋማት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም | 280 | 280 | |
| | | ማህበራዊ ሳይንስ | | | |
| | | መደበኛ እና የማታ | 290 | 280 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና ታዳጊ ክልል ተወላጅ ተማሪዎች | 280 | 280 | |
| | | ዓይነ ሥውራን | 240 | 240 | |
| | | በመንግስት መደበኛ ባለሆነ ፕሮግራምና በግል | 280 | 280 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ከ/ት ተቋማት መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም | | | |
| | | **ተፈጥሮ ሳይንስ** | | | |
| | | መደበኛ እና የማታ | 290 | 280 | |
| 2003 ዓ.ም | 2004 ዓ.ም | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 280 | 280 | |
| | | ዓይነ ስውራን | የለም | የለም | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 295 | 295 | |
| | | ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያ ( ለቀን፤ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 265 | | |
| | | ማህበራዊ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | |
| | | መደበኛና የማታ | 290 | 280 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 280 | 280 | |
| | | ዓይነ ስውራንና መስማት የተሳናቸው | 240 | 240 | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 295 | 295 | |
| | | ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያ ( ለቀን፤ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 265 | | |
| 2004 ዓ.ም | 2005 ዓ.ም | ተፈጥሮ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | ከ700 |
| | | መደበኛና የማታ | 294 | 290 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 285 | 285 | |
| | | ዓይነ ስውራን | የለም | የለም | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 299 | 297 | |
| | | ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያ ( ለቀን፤ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 265 | | |
| | | ማህበራዊ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | |
| | | መደበኛና የማታ | 275 | 270 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 270 | 268 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 270 | 270 | |
| | | ዓይነ ስውራን | 230 | 230 | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 299 | 297 | |
| | | ለግል ዓይነ ስውራን | 256 | 256 | |
| | | ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያ ( ለቀን፤ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | | 265 | |



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2005 ዓ. ም | 2006 ዓ.ም | **ተፈጥሮ ሳይንስ** | **ወንድ** | **ሴት** | ከ700 |
| | | መደበኛና የማታ | 325 | 300 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 305 | 305 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 300 | 300 | |
| | | ዓይነ ስውራን | የለም | የለም | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 330 | 320 | |
| | | ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያ ( ለቀን፤ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 265 | | |
| | | **ማህበራዊ ሳይንስ** | **ወንድ** | **ሴት** | |
| | | መደበኛና የማታ | 285 | 280 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 275 | 270 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 270 | 270 | |
| | | ሁሉም ዓይነ ስውራን ተማሪዎች | 230 | 230 | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 290 | 290 | |
| | | ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያ ( ለቀን፤ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 265 | | |
| 2006 ዓ.ም | 2007 ዓ.ም | **ተፈጥሮ ሳይንስ** | **ወንድ** | **ሴት** | ከ700 |
| | | መደበኛና የማታ | 315 | 300 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 305 | 300 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 300 | 300 | |
| | | ዓይነ ስውራን | የለም | የለም | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 320 | 315 | |
| | | ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያ | 250 | | |
| | | **ማህበራዊ ሳይንስ** | **ወንድ** | **ሴት** | |
| | | መደበኛና የማታ | 280 | 270 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 275 | 270 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 270 | 270 | |
| | | ሁሉም ዓይነ ስውራን ተማሪዎች | 230 | 230 | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 285 | 282 | |
| | | ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያ( ለቀን፤ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 250 | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ለአይነ ስውራን ተማሪሪዎች/ተፈታኞች ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያ( ለቀን፤ ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 230 | | |
| 2007 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም | ተፈጥሮ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | ከ700 |
| | | መደበኛና የማታ | 343 | 320 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 332 | 317 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 297 | 297 | |
| | | ዓይነ ስውራን | የለም | የለም | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 353 | 331 | |
| | | ለግልም ሆነ ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍለው ለሚማሩ መግቢያ( ለቀን፤ ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 275 | | |
| | | ማህበራዊ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | |
| | | መደበኛና የማታ | 322 | 302 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 310 | 295 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 275 | 275 | |
| | | ሁሉም ዓይነ ስውራን ተማሪዎች | 230 | 230 | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 330 | 310 | |
| | | ለግልም ሆነ ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍለው ለሚማሩ መግቢያ( ለቀን፤ ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 275 | | |
| 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | ተፈጥሮ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | ከ700 |
| | | መደበኛና የማታ | 354 | 340 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 340 | 335 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 297 | 297 | |
| | | ዓይነ ስውራን | የለም | የለም | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 360 | 355 | |
| | | ለግልም ሆነ ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍለው ለሚማሩ መግቢያ( ለቀን፤ ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 295 | | |
| | | ማህበራዊ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | |
| | | መደበኛና የማታ | 330 | 320 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 320 | 315 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 275 | 275 | |
| | | ሁሉም ዓይነ ስውራን ተማሪዎች | 200 | 200 | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 360 | 355 | |
| | | ለግልም ሆነ ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍለው ለሚማሩ መግቢያ( ለቀን፤ ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 295 | 295 | |
| 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም | ተፈጥሮ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | ከ700 |
| | | መደበኛና የማታ | 352 | 330 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 320 | 305 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 275 | 275 | |
| | | ዓይነ ስውራን | የለም | የለም | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 360 | 355 | |
| | | ለግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያ ( ለቀን፤ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 295 | 295 | |
| | | ማህበራዊ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | |
| | | መደበኛና የማታ | 335 | 320 | |
| | | የአርብቶ አደር ልጆችና የታዳጊ ክልል ተወላጆች ተማሪዎች | 315 | 300 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 275 | 275 | |
| | | ሁሉም ዓይነ ስውራን ተማሪዎች | 200 | 200 | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 360 | 355 | |
| | | ለግልም ሆነ ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍለው ለሚማሩ መግቢያ( ለቀን፤ ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 295 | 295 | |
| 2010 ዓ.ም | 2011 ዓ.ም | ተፈጥሮ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | ከ700 |
| | | መደበኛና የማታ | 362 | 345 | |
| | | የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ተወላጅ ተማሪዎች፣ የታዳጊ ክልል ተማሪዎች እና በፀጥታ ምክንያት ትኩረት የተሰጣቸው (የጉጅና ጌድዮ ዞን) ተማሪዎች | 345 | 330 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 275 | 265 | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 375 | 370 | |



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ለግልም ሆነ ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍለው ለሚማሩ መግቢያ( ለቀን፤ ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 295 | | |
| | | **ማህበራዊ ሳይንስ** | **ወንድ** | **ሴት** | |
| | | መደበኛና የማታ | 345 | 335 | |
| | | የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ተወላጅ ተማሪዎች፣ የታዳጊ ክልል ተማሪዎች እና በፀጥታ ምክንያት ትኩረት የተሰጣቸው (የጉጅና ጌድዮ ዞን ) ተማሪዎች | 335 | 320 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 275 | 265 | |
| | | ሁሉም ዓይነ ስውራን ተማሪዎች | 210 | 200 | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 375 | 370 | |
| | | ለግልም ሆነ ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍለው ለሚማሩ መግቢያ( ለቀን፤ ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 295 | | |
| 2011 ዓ.ም | 2012 ዓ.ም | **ተፈጥሮ ሳይንስ** | **ወንድ** | **ሴት** | ከ400 ሆኖ የሚያዙ የት/ም አይነቶች፡ Eng, Apt, Math, Phy, and Geo ብቻ |
| | | መደበኛና የማታ | 176 | 166 | |
| | | የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ተወላጅ ተማሪዎች፣ (ANGETU(R), ASEBOT(R), AWURADA(R) , BACHUMA(R) , BAREDA(R) , BIDRE(R) , BIFTU MILLINIEUM (R) , BORBOR(R), BORDODE(R) , BULBUL(R) , CHELCHEL(R) , CHINAKSEN(R), DANDI GUDINA(R), DARME(R) , DILO(R), DUBLUK(R) , ELWAYE(R), ERBANNO(R), FINCHAWA (WEST GUJI)(R) , HAREKELO(R) , HARENFEMA(R), HIDI LOLA(R), HUSSE(R), JIBRI(R), MAJI LEWT FRE(R), MALKA SODA(R), MEGGA(R), MELES ZENAWI METASEB.(R), MELKA MICHA(R) , MENA(R), MERTI(R), META GEFERSA(R) , MIDEGATOLA(R) , MILAMI(R), MIOO(R), MIZAN TEFERI(R), MOYALE(R), NEGELLE(R) , SHOA BENCH(R), TAYFE(R) , WADERA(R) and YABELLO(R) | 166 | 156 | |

| | | |
|---|---|---|
| የአፋር፣ ሶማሊያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ጋምቤላ ክልል ተማሪዎች | 166 | 156 |
| በፀጥታ ምክንያት ትኩረት የተሰጣቸው አካባቢ ተማሪዎች፡ Wolega East Zone ( HARO LIMU®, HINDE®, LIMU GALILA® , BALO®) , Wolega West Zone (BABO GEMBEL(R, BEGHI®, SENA GENJI®, GULISO®, KONDALA®, BIKILTU DEBASO®, YUBDO®)፣ Kelem Wolega (ANFILO®, DALE SADI®, KELEM®, KAKE®, KEBE®, BIFTU GIDAMI®, JIMMA®, GELAN (GEBA ROBI)®, LALO KILE®, CHANKA®, ALEKU®, GUDINA SEYO®, TEJO®)፣ Borena Zone (BORBOR(R), DUBLUK(R) , DILO®, HIDI LOLA(R), ELWAYE(R), MEGGA(R), META GEFERSA(R) , MILAMI(R), MOYALE®)፣ Guji Zone (BULBUL(R) , DARME(R) , HAREKELO®, FINCHAWA (WEST GUJI)(R) , MALKA SODA(R), MEGADO®, BULEHORA®, TORE®)፣ Bole Zone (BIDRE(R), JIBRI(R), MIOO®)፣ Hararge East Zone (CHINAKSEN®, BABILE(E.HARERGE®, GURSUM(E.HARARGIE®፣)፣ Hararge West Zone (DOBA®, BORDODE®, RIMETI®, MESELA®, ASEBOT®) | | |
| የፈተና አሰጣት ችግር ያለበት ት/ቤት(HAWARIYAT®) | 166 | 156 |
| ሁሉም መስማት የተሳናቸው | 120 | 115 |
| የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 190 | 185 |
| ለግልም ሆነ ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍለው ለሚማሩ መግቢያ( ለቀን፤ ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | | 140 |
| **ማህበራዊ ሳይንስ** | **ወንድ** | **ሴት** |
| መደበኛና የማታ | 174 | 164 |



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ተወላጅ ተማሪዎች፣ (ANGETU(R),ASEBOT(R), AWURADA(R) , BACHUMA(R) , BAREDA(R) , BIDRE(R) , BIFTU MILLINIEUM (R) , BORBOR(R), BORDODE(R) , BULBUL(R) , CHELCHEL(R) , CHINAKSEN(R), DANDI GUDINA(R), DARME(R) , DILO(R), DUBLUK(R) , ELWAYE(R), ERBANNO(R), FINCHAWA (WEST GUJI)(R) , HAREKELO(R) , HARENFEMA(R), HIDI LOLA(R), HUSSE(R), JIBRI(R), MAJI LEWT FRE(R), MALKA SODA(R), MEGGA(R), MELES ZENAWI METASEB.(R), MELKA MICHA(R) , MENA(R), MERTI(R), META GEFERSA(R) , MIDEGATOLA(R) , MILAMI(R), MIOO(R), MIZAN TEFERI(R), MOYALE(R), NEGELLE(R) , SHOA BENCH(R), TAYFE(R) , WADERA(R) and YABELLO(R)) | 164 | 154 | |
| | | የአፋር፣ ሶማሊያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ጋምቤላ ክልል ተማሪዎች | 164 | 154 | |
| | | በፀጥታ ምክንያት ትኩረት የተሰጣቸው አካባቢ ተማሪዎች፡ Wolega East Zone ( HARO LIMU®, HINDE®, LIMU GALILA® , BALO®) , Wolega West Zone (BABO GEMBEL(R, | 164 | 154 | |



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | BEGHI®, SENA GENJI®, GULISO®, KONDALA®, BIKILTU DEBASO®, YUBDO®)፣ Kelem Wolega (ANFILO®, DALE SADI®, KELEM®, KAKE®, KEBE®, BIFTU GIDAMI®, JIMMA®, GELAN (GEBA ROBI)®, LALO KILE®, CHANKA®, ALEKU®, GUDINA SEYO®, TEJO®)፣<br>BorenaZone (BORBOR(R), DUBLUK(R) , DILO®, HIDI LOLA(R), ELWAYE(R), MEGGA(R), META GEFERSA(R) , MILAMI(R), MOYALE®)፣<br>Guji Zone (BULBUL(R) , DARME(R) , HAREKELO®, FINCHAWA (WEST GUJI)(R) , MALKA SODA(R), MEGADO®, BULEHORA®, TORE®)፣<br>BoleZone (BIDRE(R), JIBRI(R), MIOO®)፣ Hararge East Zone (CHINAKSEN®, BABILE(E.HARERGE®, GURSUM(E.HARARGIE®፣)፣<br>Hararge West Zone (DOBA®, BORDODE®, RIMETI®, MESELA®, ASEBOT®) | | | |
| | | የፈተና አሰጣት ችግር ያለበት ት/ቤት(HAWARIYAT®) | 164 | 154 | |
| | | ሁሉም መስማት የተሳናቸው | | 140 | |
| | | ሁሉም አይነ ስውራን | 90 | 85 | |
| | | የግል ተፈታኝ ተማሪዎች | 190 | 185 | |
| | | ለግልም ሆነ ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍለው ለሚማሩ መግቢያ( ለቀን፤ለማታ እና ለርቀት ትምህርት) | 140 | | |
| 2013 ዓ.ም | 2014 ዓ.ም | 1ኛ ዙር ተፈጥሮ ሳይንስ | ወንድ | ሴት | 600 |
| | | መደበኛና የማታ | 363 | 351 | |
| | | ታዳጊ ክልልና አርብቶ አደር | 351 | 339 | |
| | | መስማት ለተሳናቸው | 300 | 300 | |
| | | የግል ተፈታኝ | 380 | 380 | |

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፖ. ሳ. ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ ከተማ,
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ጥቅምት 06 2018
ቁጥር/REF NO: 9/247/566/18

ለሁሉም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የ2018 የትምህርት ዘመን የአቅም ማሻሻያ ፕሮግራም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን ይመለከታል</u>

በ2017 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ማጠቃለያ ፈተና ወስደው በ2018 የትምህርት ዘመን ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመግባት የአቅም ማሻሻያ ፕሮግራም ለመውሰድ የመግቢያ ውጤት መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት መሆኑን እናሳውቃለን።

| ተ.ቁ | መግለጫ | ጠቅላላ ውጤት | የመግቢያ መቁረጫ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | የተፈጥሮ እና ማህበራዊ ሳይንስ ወንድ ተማሪዎች | 600 | 216 |
| 2 | የተፈጥሮ እና ማህበራዊ ሳይንስ ሴት ተማሪዎች | 600 | 204 |
| 3 | ታዳጊ ክልሎች እና የአርብቶ አደር አካባቢ የተፈጥሮ እና ማህበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች ለሁለቱም ፆታ | 600 | 198 |
| 4 | የተፈጥሮ እና ማህበራዊ ሳይንስ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ለሁለቱም ፆታ | 600 | 198 |
| 5 | የተፈጥሮ እና ማህበራዊ ሳይንስ ዓይነ ሥውራን ተማሪዎች ለሁለቱም ፆታ | 600 | 165 |

<u>ማሳሰቢያ</u>፡ የ2018 የትምህርት ዘመን የአቅም ማሻሻያ ፕሮግራም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን በተመለከተ በመንግስትም ሆነ በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ልዩነት የሌለ መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ኮራ ጡፋ ሚጀና (ዶ/ር)
የአካዳሚክ ጉዳዮች ዋና ስራ አስፈፃሚ

<u>ግልባጭ</u>

- ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ
- ለግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አገልግሎት ዴስክ
  <u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ ከተማ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ጥቅምት 20 2018

ቀን/DATE:
ቁጥር/REF NO: 1/247/6/6/18

ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች

**<u>በያሉበት</u>**

ጉዳዩ፡- **የ2018 ትምህርት ዘመን ወደ ከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ውጤትን ይመለከታል፤**

የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተማሪዎች ወደቀጣይ የትምህርት ደረጃ ለመሻገር 50 በመቶና በላይ ማምጣት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2017 የትምህርት ዘመን በኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሠርቲፊኬት (12ኛ ክፍል) ፈተና በአማካይ ውጤታቸው 49.50 — 49.99 በመቶ ያመጡ ተማሪዎች ውጤታቸው ወደ 50 በመቶ የሚጠጋጋ በመሆኑ 49.50 እና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ዝቅተኛውን 50 በመቶ የማለፊያ ነጥብ ያሟሉ ሆኖ የተወሰነ መሆኑ ታውቆ ወደ ከፍተኛ ትምህርት በመግባት መማር እንዲችሉ ተገቢው ሁሉ እንዲፈጸም አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

**ግልባጭ፡-**

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት

  **ትምህርት ሚኒስቴር**

- ለሁሉም ክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎች

  **በያሉበት**

- ለትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት

  **አዲስ አበባ**

- ለትምህርትና ሥልጠና ባለስልጣን

  **አዲስ አበባ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education

በኢፌዲሪ የትምህርትና ስልጠና ባለሥልጣን
FDRE EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

## ከኢፌዲሪ የትምህርትና ስልጠና ባለሥልጣን የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መስፈርቶችን በተመለከተ የተሰጠ ማሳሰቢያ

በቅድመ-ምረቃ እና በድህረ-ምረቃ መርሃ-ግብር ተመዝጋቢዎች የሚከተሉትን የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡-

☛የትምህርት ሚኒስቴር ለትምህርት ዘመኑ ያሳውቀውን የከፍተኛ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ መግቢያ መስፈርት የመቁረጫ ነጥብ አሟልተው መገኘት አለባቸው፤

☛ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም የተመረቁ ባለሙያዎች በከፍተኛ ትምህርት በቅድመ-ምረቃ ደረጃ ለመመዝገብ በሠለጠኑበት የሙያ መስክ በደረጃ 4 ወይንም በቀድሞ 10+3 ወይንም 12+2 ዲፕሎማ ያጠናቀቁ ሆነው በሙያው ደረጃ 4 የብቃት ማረጋገጫ ምዘና (COC level 4) ተፈትነው ያለፉበትን ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤

☛ለ2ኛ ዲግሪ ተመዝጋቢዎች በባለሥልጣኑ ህጋዊነቱ የተረጋገጠ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፤ እንዲሁም National Graduate Admission Test (NGAT) የማለፊያ ውጤት ያላቸው መሆን አለባቸው ፡፡

☛ከውጭ ሀገር የተገኘ የትምህርት ማስረጃ ለመግቢያ መስፈርት የሚያገለግለው በባለስልጣኑ የአቻ ግምት ሲሰራለት ብቻ ይሆናል፡፡

☛ከተጠቀሱ መመሪያዎች ውጪ ገብተው ለሚማሩ ኃላፊነቱ የተመዝጋቢዎቹ እና የተቋማቱ ብቻ መሆኑን እናሳስባለን።

**የኢፌዲሪ ትምህርትና ስልጠና ባለሥልጣን**

የትምህርትና ስልጠና ባለ
EDUCATION AND TRAINING AUTH